# ከ12 ዓመት በታች ለሆኑ ልጆች የፊት መሸፈኛ ጭንብል መመሪያ



የ CDC እና ዋሽንግተን እስቴት መመሪያን በመከተል ሙሉ በሙሉ የተከተቡ ነዋሪዎች ከንግዲህ በኋላ በአብዛኛው ቤት ውስጥ እና ውጪ  የፊት መሸፈኛ ጭንብል (ማስክ) መልበስ አይጠበቅባቸውም። ዕድሜያቸው ከ16 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የኪንግ ካውንቲ ነዋሪዎች በአሁኑ ሰዓት ክትባቱን 70% ያህል ሙሉ ለሙሉ ስለተከተቡ እና ስለጨረሱ ኪንግ ካውንቲ የአከባቢውን የማስክ መመሪያ አንስቷል።  በዚህ ደረጃ ክትባቱን መስጠት አስደናቂ ስኬት ነው። ይሔ ቢሆንም ከ12 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች እስካሁን ክትባት መውሰድ አልቻሉም። ይህ ማለት በኪንግ ካውንቲ ውስጥ ከ300,000 በላይ የሆኑ ልጆች ከኮቪድ-19 በሽታ አልተጠበቁም ማለት ነው።

የፊት መሸፈኛ ጭንብል አሁንም ልጆችን ለመጠበቅ ጠቃሚ መንገድ ነው። ያልተከተቡ ልጆች  ቫይረሱን ለሌሎች ማስተላለፍ ስለሚችሉ ጭንብል መልበስ ሌሎችንም ይጠብቃል። የማህበረሰባችንን ጤና ለመጠበቅ እርስ በር ሳችን ላይ መመርኮዝን እንቀጥላለን። ሁሉም አዋቂዎች በትምህርት ቤቶች እና በልጆች እንክብካቤ መስጫ ስፍራዎች ላይ የፊት መሸፈኛ ጭንብሎችን መልበስ አለባቸው።

በተጨማሪም ልጆች በብዛት በሚገኙበት ሌሎች ያህዝብ ቤቶች ውስጥ የፊት መሸፈኛ ጭንብሎችን  ለመልበስ ያስቡ።

ለወላጆች፣ ለእንክብካቤ ሰጪዎች፣ እና ለቤተሰቦች ከ 12 ዓመት በታች ያሉ ልጆችን ደህንነት የምትጠብቁባቸው መንገዶች እነዚህን ይመስላሉ።

**ለኮቪድ-19 ክትባት ብቁ ከሆኑ ክትባቱን ይውሰዱ**

**የፊት መሸፈኛ ጭንብል የመልበስ ባህሪን ማሳያት ይቀጥሉ.**

ምንም እንኳን እርስዎ እና ሌሎች የቤተሰብ አባላት ሙሉ ለሙሉ ተከትበው ቢሆንም ሁላችሁም አብራችሁ ውጪ ስትሆኑ ለልጆቻችሁ ጭንብል በመልበስ ድጋፍ አሳዩ።





**ለምን አሁንም አስፈላጊ እንደሆነ ያስረዱአቸው።**

ትናንሽ ልጆች ለምን የፊት መሸፈኛ ጭንብል ትልልቅ ልጆች እና አዋቂዎች ሳይለብሱ እነሱ መልበስ እንዳለባቸው ግራ ሊገባቸው ይችላል። ነገሮች እየተሻሻሉ ቢሆንም  የፊት መሸፈኛ ጭንብሎችን ሁሉም ሰው ክትባት እስኪከተብ ድረስ ድህንነታቸውን እደሚጠብቅ ያስረድአቸው።

## እንደ እንቅስቃሴው ዓይነት እና ሁኔታ አንጻራዊን ስጋቶች ይገምግሙ።

የያንዳንዱ ሰው የስጋት መቋቋም ችሎታ የተለያየ ነው። ዕድሜያቸው ከ 12 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች የማህበረሰብ በሽታ የማስተላለፉ አደጋዎችን እና ካልተከተቡ ሰዎች ወይም ቤተሰብ ካልሆኑ ሰዎች ጋር በቤት ውስጥ የመሳተፍ ተጽዕኖዎችን ማስተዋል አለባቸው። በተጨማሪም የአካል ርቀት የመጠበቅ ዕድልን እንዲሁም በተከታታይ የፊት መሸፈኛ ጭንብል መልበስን ሁኔታ ማሰብ አለባቸው።

## በሚችሉበት ጊዜ ሁሉ ውጪን ይምረጡ

ኮቪድ-19 የመስፋፋት አደጋ ከቤት ውስጥ ውጪ ያንሳል።.

## የቤተሰብ ዕቅድ ያዘጋጁ ።

ቤተሰብዎ እና ትናንሽ ልጆችዎ  የፊት መሸፈኛ ጭንብል በሚለብሱ እና በማይለብሱ  የሰዎች ቡድኖች ጋር ብዙ ጌዜ ማሳለፍ ሲጀምሩ፤ ለተለያዩ ስብሰቦች እና ስፍራዎች ዕቅድ ማውጣት ለልጆጆት ምን እንደሚጠበቅባቸው እንዲያውቁ ይረዳቸዋል።

- ከቅርብ እና የሩቅ ቤተሰቦት ጋር ስለ የስጋት ምዘናን እና ስለ ጤንነት ታሪክ በግልጽ ይወያዩ። ልጆች በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ምን እንደሚጠበቅባቸው እንድያውቁ እና የተለመደውን አሰራር
- እንዲተባበሩ ጽኑ ይሁኑ።

  ለምሳሌ ዕቅድዎ እነዚህን ሊመስል ይችላል፥
-
  - ክትባት ከተከተቡ ቤተሰቦች ጋር አብሮ ለመሆን የፊት መሸፈኛ ጭንብል አይልበሱ፣ ነገር ግን የሸቀጣሸቀጥ ሱቆች እና ሌሎች የግብይት ቦታዎች ሲሄዱ ሁሉም ህጻናት እና አዋቂዎች የፊት መሸፈኛ ጭንብል ይልበሱ ።
  - ከቤት ውጪ ከጓደኞቻቸው ጋር ለመጫወት የፊት መሸፈኛ ጭንብል መልበስ አይልበሱ፣ ነገር ግን ሰው በበዘበት መጨወቻ ቦታዎች ላይ ወይም እቤት ለመጫወት የፊት መሸፈኛ ጭንብል እንዲለብሱ ያድርጉ።
  - ትንሽ፣ የቅርብ ጓደኞቻቸው ጋር፣ ልጆቹ ባይከተቡም ከቤት ውስጥ ወይም ውጭ አብሮ ለማሳለፍ የፊት መሸፈኛ ጭንብል መልበስ አያስፈልጋቸውም (አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ቡድኖች እንደ  ልዩ ማህበራዊ ስብስብ ይቆጠራሉ) ።

ለበለጠ መረጃ ይህን ድህረገፅ ይጉብኙ:
**KINGCOUNTY.GOV/VACCINE/YOUTH**

Public Health
Seattle & King County